# ወገኔ ኦባማ

ዓለምን ያቀፈ ወገኔ ኦባማ፤
ፍጹም ልዩ የሆነ ከሁሉ የሚስማማ።
እናት ከአሜሪካ አባቱ ከኬንያ፤
በህጻንነቱ አደገ በኢንዶኔዢያ።
ትምህርቱን ቀጠለ በሐዋይ ደሴት፤
ከሚፍለቀለቀው ከእሳቱ መሬት።
የተማሪ አለቃ በሃርቫርድ ኮሌጅ፤
ተደናቂው ጥቁር የመጀመሪያው ልጅ።
ታሪክ ሰሪው ወጣት ቺካጎ ሄደና፤
ድሃውን ለመርዳት በዳውንታውን ጎዳና፤
የፈረሰውን ቤት ለሁሉም አቀና።
ወርቅ የሆነች ልጅ በዚሁ ከተማ፤
አግብቶ ሰየማት ሚሼል ኦባማ።
ሴኔተር ኦባማ ተብሎ ተሾመና፤
ብርቅየው ጎልማሳ ካፒቶል ገባና፤
ሥራውን ጀመረ አገሩን ሊያቀና።
ሠላም ሠላም ሠላም ጦርነቱ ይብቃ፤
የአለም ሰው ሞቱ ጭራሽ እንዲበቃ።
አልፈርምም አለ ይብቃ ጦርነት፤
ኤኮኖሚያችንን ጭራሽ የሚያንኮታኩት።
ጭንቅላቱ ንጹህ ጥላቻም የለው፤
ተንኮል ሲታሰብበት ፍጹም አይከፋው።

ሁሉም ይቻላል መፈክሩ ነው፣
ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ የማይለው።
ዘሩ ከኬንያዊ የአፍሪካ አንበሣ፣
ጥቁርን አስጠሪ ለሁሉ የሚያገሳ።
ስድስት ቀን የቀረው ወንድሜ ባራክ፣
ዝናብ ሳይበግረው ለቸነፈር ሳይንበረከክ፣
አደራ ሰጥቶናል እንዳይመጣ መብረክረክ፣
እጃችንን እንዳንሰጥ ለመኬን መድረክ።
በዓለም ታሪክ ውስጥ አድዋን አስታውስ፣
ጥቁር አሸንፎ እንዳለን ደስ ደስ።
ኦባማም በተራው ታሪክ ይሰራና፣
ከታሪክ ማህደር ውስጥ ይቀመጥና፣
ከማጎንበስ ይልቅ እንላለን ቀና።
ኢትዮ-አሜሪካዊ ሲትዝን የሆንከው፣
ቀኑ ደረሰልህ ላንተ የሆነ ሰው፣
ጥቁርነትህን ሊያኮራ ነው የተነሳው፣
ወንድምህን ወጥተህ በኩራት ምረጠው፣
ኦባማ ነውና ለሁሉ የሚበጀው።
በኖቬምብር አራት ታሪክ ይሰራል፣
የመጀመሪያው ጥቁር ወንበር ይጨብጣል።
እግዚአብሔር ይባርክህ አይዞህ ወንድማችን፣
እድልህን ያቅናው የእኛው መመኪያችን።

ተገጠመ፣ በመልካሙ ካሣሁን

Oct 29, 2008